# የትግራይ ወያኔ አዜብ መስፍን ከማዕከላዊ ኮሚቴ አባልነተ አባረረ፣ አባይ ወልዱን ወደታች አወረደ!

**የህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ ፅ/ት ቤት /ህ.ወ.ሓ.ት/**

**Tigray People's Liberation Front Head office /TPLF/**

የህወሓት ማእከላይ ኮሚቴ አመራሩ ያለበትን ሁኔታ በመገምገም ጥልቀት ያለው የሂስና ግለሂስ መድረክ እንደከፈተ ይታወቃል። በድርጅቱ አመራር ዘንድ ከመድረካዊ ተልእኮ አፈፃፀም ጋር በተያዘ የታዩ ስር የሰደዱ ድክመቶችን በጥልቀት የገመገመው ማእከላይ ኮሚቴው የድክመቱ የከፋ ጫፍ የሆነውን ስራ አስፈፃሚ እንደ አካልም ሆነ እንደ ግለሰብ አባላት በመገምገም የእርምት እርምጃዎችን ወስዷል። በዚህ መሠረት ከስራ አስፈፃሚው አባላት መካከል የድርጅቱ ሊቀመበር **አቶ ኣባይ ወልዱ** እና የስራ አስፈፃሚ አባል **አቶ በየነ ምክሩ** ወደ ማእከላይ ኮሚቴ አባልነት ዝቅ ብለው እንዲሰሩ ወስነዋል። የድርጅቱ ስራ አስፈፃሚ አባል የሆኑት **ጓዲት አዜብ መስፍን** ከማእከላይ ኮሚቴ ታግደው እንዲቆዩ ተወስነዋል። ከዚህ በተጨማሪ ለሁለት የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ማስጠንቀቅያ ሰጥቷል ።

ማእከላይ ኮሚቴው በቀሪው ማእከላይ ኮሚቴ አባላት ላይ ጥልቅ ሂስና ግለሂስ እየቀጠለ ሲሆን በአጭር ጊዜ ውስጥ በማጠናቀቅ የአመራር መልሶ ማደራጀት የሚያደርግ ይሆናል ።

**የህወሓት ማእከላይ ኮሚቴ ፅ/ት ቤት!**

Horn Affairs